# በሁሉም ነቢያት ዘንድ ሲነገርለት የቆየ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመላ ዓለም የተሰጠ በረከት

በመጽሐፍ ቅዱስና
በቁርአን በተሰፋ
የተጠበቀው
መሢሕ

ትራክት 1

## ሕያውና ዘለዓለማዊ በሆነው አምላክ ስም

ውድ አንባቢ ሆይ፤

ይህች ትንሽ መጽሐፍ በዚሁ መልኩ የተዘጋጀችው የሚከተሉትን ነገሮች ለማሳየት ነው፤ እነርሱም እንደሚከተለው ይዘረዘራሉ፡-

- እግዚአብሔር ፍጹም መሆኑን እና የሚሠራውም በፍጹምነት መሆኑን ነው።
- እግዚአብሔር መላ ዓለምን ለመባረክ ፍጹም የሆነ ዕቅድ አለው።
- እግዚአብሔር ይህን ዕቅዱን ባንዳፍታ ማሳወቅ ሳይሆን ቀስ በቀስ መግለጡን ነው።
- እግዚአብሔር ዕቅዱን መግለጥ ከጀመረ ከ4000 ዓመታት በላይ መሆኑን ነው።
- እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ዕቅዱን በመጽሐፍ ማስፈሩን ነው።
- የእግዚአብሔር ዕቅድ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሠፍረው መገኘታቸውን ነው።
- እግዚአብሔር ዕቅዱንና በረከቱን ሁሉም ሰው እንዲያውቅ መፈለጉን ነው።

«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38 ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

## ክፍል 1፡- የቁርአን ምስክርነት

በምዕራፍ 3 ዓሊ-ዒምራን 45 የተጻፈው እንዲህ ይነበባል፡-

> «መላእክት ያሉትን (አስታውስ)፡- መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በኾነው ቃል፥ ስሙ አልመሲሕ ዒሳ የመርየም ልጅ፥ በዚህ ዓለምና በመጨረሻውም ዓለም የተከበረ፥ ከባለሟሎችም በኾነ (ልጅ) ያበስርሻል፤»

ስለዚህ ቁርአን ኢየሱስን መሢሕ እንደሆነ በይፋ ያስቀምጣል። ኢየሱስን አሥራ አንድ ጊዜም መሢሕ ሲል ቀጽሎታል። ይሁንና የመሢሕን ትርጉም ገልጾ አያስቀምጥም። ስለዚህ ከቁርአን ውጪ ሌሎችን መጻሕፍት መቃኘት ይኖርብናል። ከዚሁ ስም ጋር የተቆራኘውን በረከትም ሆነ ደማቅ ስፍራ ማጤን ያስችለናል።

ቁርአን ከመጻፉ ከበርካታ ዓመታት በፊት የነበሩ ቅዱሳት መጻሕፍት (ብሉይና ሐዲስ ኪዳን) በመሢሑ በኩል ይገለጥ ዘንድ ያለውን የተስፋ ቃል አካተው ይዘዋል። ቁርአንም እነዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት ከእግዚአብሔር የተሰጡ ለመሆናቸው በማረጋገጥ ጽፏል። ቁርአን በዚሁ ላይ ያለውን ብናነብ፡-

> «ሙሳንም መጽሐፍን (ተውራትን) በእርግጥ ሰጠነው...» በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን)፥ (ምዕ.2 አል-በቀራህ 87።) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዔልና ወደ ኢስሐቅም፥ ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም፥ በተዋረደው፥ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፥ በዚያ ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት፥... አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ። (ምዕራፍ 2፡ አል-በቀራህ 136) ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው (ምዕራፍ 4፡ አል-ኒሳእ 163)።
>
> «በፈለጎቻቸውም (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን፥ ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን፥ አስከተልን፤ ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት፥ በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ፥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሣጭ ሲኾን ሰጠነው» (ምዕራፍ 5፥ አል-ማኢዳህ 46)።
>
> በተጨማሪም ቁርአን ከብዙ ዓመታት በፊት የነበሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን (በብሉይና አዲስ ኪዳን)

ይታመኑ ዘንድ ያግባባል። በዚሁ ላይ ቁርአንን ብንጠቅስ፡-

«እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህና ...በዚያም በመልእክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ... እመኑ፤» (ምዕራፍ 4፡ አል-ኒሳእ 136)።

ይሁንና ቅዱሳት መጻሕፍትን (ብሉይና አዲስ ኪዳን) እናምን ዘንድ መጻሕፍቱን ጠንቅቆ ማወቁ ቀዳሚ ተግባር ይሆናል፤ ስለዚህ መጻሕፍቱ መሢሑ ለምንና እንዴት ለመላ ዓለም የመጣ የእግዚአብሔር በረከት እንደሆነ የሚቀጥሉትን ገጾች እንመለከታለን።



## ክፍል 2፡- በመጽሐፍ ቅዱስ የሠፈረው የመሢሑ ማንነት

በሕግጋተ ሙሴና (ቶራኽ) በመዝሙረ ዳዊት (ዘቡር) እና በነቢያትም እንደተነገረው እግዚአብሔር ልዩ ሰው የሆነውን መሢሕ እንደሚልክ የተስፋ ቃል ሰጠ።

### <u>የመሢሑ የዘር ሐረግ</u>

አዳም

በመጽሐፈ ሕግጋት (ቶራኽ) እንደተጻፈው በአዳምና ሔዋን ዘመን እግዚአብሔር በእባብ የተመሰለውን ሰይጣን እንዲህ አለው፡-

1) «በአንተና <u>በሴቲቱ</u> መካከል፥ በዘርህና <u>ዘርዋም</u> መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤»

2) «<u>እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል</u>፥»

3) «<u>አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ</u>»
(ኦሪት ዘፍጥረት 3፡15)።

<u>ኖህ</u>

2000 ዓመታት ከኢየሱስ በፊት

<u>አብርሃም</u>
<u>ይስሐቅ</u>
<u>ያዕቆብ</u>

በቶራኽ እግዚአብሔር ለአብርሃም፥ ይስሐቅና ለያዕቆብ እንዲህ ሲል ተናገረ፡-

4) «<u>በዘርህም</u>...

5) «<u>የምድር አሕዛብ... ሁሉም ይባረካሉ</u>፥
(ኦሪት ዘፍጥረት 22፡18፤ 26፡4፤ 28፡14)።

1 0 0 0 ዓመታት ከኢየሱስ በፊት

ዳዊት፡-

(በዘቡር) እንደሚነበበው እግዚአብሔር ለዳዊት እንዲህ ብሎታል፡-
«ዳዊትን እንዳልዋሸው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ።

6) «<u>ዘሩ ለዘለዓለም</u>፥

7)«<u>ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል</u>። <u>ለዘለዓለም እንደ ጨረቃ ይጸናል</u>፤» (መዝሙረ ዳዊት 89፡35-37)።

ኢየሱስ፡-

በኢንጅል (አዲስ ኪዳን) እንደተጻፈው፥ ቀደም ሲል የተሠመረባቸው ሰባቱ የትንቢት ክፍሎች ተፈጻሚነታቸው በአንድ ሰው በኩል ተገልጸዋል። እያንዳንዱን በዝርዝር ስንመለከታቸው፡-

1) ኢየሱስ የተወለደው ከሴት ዘር እንጂ ከወንድ ዘር አይደለም። ሐዋርያው ማቴዎስ እንደጻፈው፡-
«የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች (ማቴዎስ 1፡18)።

2) ኢየሱስ በሞቱ ዲያብሎስን አቅም የለሽ አደረገ፤ ራሱንም ለመቀጥቀጥ ቻለ። በዚሁ ላይ ኢንጅልን ብንጠቅስ፡-

«እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥» (ዕብራውያን 2፡14)።

3) ዲያብሎስ ይሁዳን በመገፋፋት ኢየሱስን ይከድ ዘንድ በማድረጉ እንደቀጠቀጠው ያህል ይወሰዳል። ሐዋሪያው ዮሐንስ የጻፈውን ብናነብ፡-

«እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥ . . .» (ዮሐንስ 13፡2)።

4) ኢየሱስ ከአብርሃም ከይስሐቅና ከያዕቆብ ዘር ተወለደ። ሐዋርያው ማቴዎስ ስለዚህ የሚከተለውን ጽፏል፡-

«የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ . . .» (ማቴዎስ 1፡1-2)።

5) ኢየሱስ ሰዎችን ከአሕዛብ ሁሉ በደሙ የዋጀ የእግዚአብሔር በረከት ነው። ስለዚህ እውነት ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ጽፏል፡-

«መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ . . .» (ራእይ 5፡9)።



6) ኢየሱስ የተወለደው ከዳዊት ዘር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ዘር ሲጽፍ እንዲህ ይላል፡-
«በወንጌል እንደምሰብከው፡ ከሙታን የተነሣውን ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤ ...» (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡8)።

7) ኢየሱስ ንጉሥ ሆኖ ተወልዷል። ንግሥናውም የዘለዓለም ይሆናል። የኢየሱስ ሐዋርያት ወገን የሆነው ሉቃስ ቅዱስ ገብርኤል ለማርያም የነገራትን ብሥራት ገልጾ በጻፈው፡-

«እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። . . . አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ . . . ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም» (ሉቃስ 1፡31-33)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረው የመሢሑ መወለድ...

መሢሑ በቤተልሔም ይወለዳል:

ነቢዩ ሚክያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክያስ 5፡2)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁም፥ ከ700 ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሐዋርያው ማቴዎስ እንዲህ ጽፏል:-

> «ኢየሱስ በይሁዳ ቤተ ልሔም... በተወለደ ጊዜ፥ ... አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሽም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና (ማቴዎስ 2፡1፤ 5፤ 6)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረው የመሢሑ መወለድ...

የመሢሑ አመጣጥ ከጥንት፥ ከዘለዓለም ነው:

ነቢዩ ሚክያስ ከጻፈው ብንመለከት:-

> «...አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል» (ሚክያስ 5፡2)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንደገና፥ ከ 700 ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:- ኢየሱስ በጸሎት ያነሣቸውን ሐዋርያው ዮሐንስ በኢንጅል ያሰፈረውን ስንመለከት:-

> «አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ» (ዮሐንስ 17፡5)።



## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረው የመሢሑ መወለድ...

መሢሑ ከድንግል ይወለዳል መሢሑ አማኑኤል ተብሎ ይጠራል፤ ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ነው።

ነቢዩ ኢሳይያስ ስለዚሁ ሲጽፍ:-

> «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» (ኢሳይያስ 7፡14)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

አሁንም፥ ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ማቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፏል:-

> «...እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ:- የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢዩ ከጌታ ዘንድ:- እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙን አማኑኤል ይሉታል። የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም:- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።» (ማቴዎስ 1፡20-23)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረው የመሢሑ መወለድ...

የመሢሑ ስም አማኑኤል ይባላል እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው! የሚልም ትርጉም አለው።

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ጽፏል:-

> «እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ኢሳይያስ 7:14

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

አሁንም ከ700 ዓመታት እንደ ኢንጅሉ መሠረት:- ኢየሱስ «ቃል» ተብሎአል። በዚሁ ላይ ሐዋርያው ዮሐንስም እንዲህ ጽፏል:-

> «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን» (ዮሐንስ 1:1፤14)።



## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረ የመሢሑ ሥቃይ...

ያለ አንዳች ምክንያት በመሢሑ ላይ በርካታ ጠላቶች ይነሱበታል፡ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ጽፏል:-

> «በከንቱ የሚጠሉኝ ከራሴ ጠጉር በዙ፤ በዓመፅ የሚያሳድዱኝ ጠላቶቼ በረቱ...» (መዝሙረ ዳዊት [69]:4)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁም፥ ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ኢየሱስ እንዲህ አለ:-

> «እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል። ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ስላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል። ነገር ግን በሕጋቸው:- በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው» (ዮሐንስ 15:23-25)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገር የመሢሑ ሥቃይ...

መሢሑ በገዛ ጓደኛው ይከዳል:

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ጽፏል:-

> «...የታመንሁበት እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ» (መዝሙረ ዳዊት [41]:9)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

አሁንም፥ ከሺህ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ኢየሱስ እንዲህ አለ:-

> «...እኔ የመረጥኋቸውን አውቃለሁ፤ ነገር ግን መጽሐፍ:- እንጀራዬን የሚበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣብኝ ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው። በሆነ ጊዜ እኔ እንደሆንሁ ታምኑ ዘንድ፥ ከአሁን ጀምሬ አስቀድሞ ሳይሆን እነግራችኋለሁ። ...እውነት እውነት እላችኋለሁ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል... እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ:- ጌታ ሆይ፥ ማን ነው? አለው። ኢየሱስም:- እኔ ቁራሽ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው ብሎ መለሰለት። ቁራሹም አጥቅሶ ለአስቆሮቱ ለስምዖን ልጅ ለይሁዳ ሰጠው» (ዮሐንስ 13:18፥ 19፥ 21፥ 25፥ 26)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረ የመሢሑ ሥቃይ...

በመሢሑ ላይ ይተፋበታል:

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «...ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም» (ኢሳያስ 50:6)።

## በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁም፥ ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላ በኢንጅሉ መሠረት:

ሉቃስ ምስክርነቱን ሰጠ:-

> «አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው:- እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል። ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል፥ ይተፉበትማል፤...» (ሉቃስ 18:31፥32)።

## አስቀድሞ በነቢያት የተነገረ የመሢሑ ሥቃይ...

መሢሑ ከሕግ ተላላፊዎች ጋር ይቆጠራል:

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «...ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና...» (ኢሳይያስ 53:12)።

## በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁም፥ ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ማርቆስ እንዲህ ሲል ጽፏል:-

> «ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዶች አንዱን በቀኙ አንዱንም በግራው ሰቀሉ። መጽሐፍም:- ከዓመፀኞች ጋር ተቈጠረ ያለው ተፈጸመ» (ማርቆስ 15:27፥28)።



## ነቢያት በመሢሑ መሞት ላይ የተናገሩትን በተመለከተ...

መሢሑ ለሰዎች ኃጢአት ሲል የሚሞት መሆኑን:

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤... እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።... ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር ... ተወገደ።... ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፥ ዕድሜውም ይረዝማል፥... ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውንም ይሸከማል።... የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥...» (ኢሳይያስ 53:5፥ 6፥ 8፥ 10፥ 11፥ 12)

## በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁም፥ ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ኢየሱስ እንዲህ አለ:-

> «...የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» (ማቴዎስ 20:28)።

በዚሁ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈውን ብንመለከት:-

> «መጽሐፍም እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም» ብሎአል (1ኛ ቆሮ. 15:3)።

## ነቢያት በመሢሑ መሞት ላይ የተናገሩትን በተመለከተ...

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ጽፏል:- ከመሢሑ አጥንቶች አንዱ እንኳ አይሰበርም

> «እግዚአብሔር አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል፥ ከእነርሱም አንድ አይሰበርም» (መዝሙረ ዳዊት [34]፡20)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንደገና፥ ከአንድ ሺ ዓመት በፊት እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሐዋርያው ዮሐንስ እንዲህ ጽፏል:-

> «ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤ ...ይህ የሆነ:- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው» (ዮሐንስ 19፡32፥ 33፥ 36)።

## ነቢያት በመሢሑ መሞት ላይ የተናገሩትን በተመለከተ...

መሢሑ ይወጋል:

ነቢዩ ዘካርያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «...ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ» (ዘካርያስ 12፡10)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንደዚሁ፥ ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሐዋርያው ዮሐንስ ጽፏል:-

> «ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።... ደግሞም ሌላው መጽሐፍ:- የወጉትን ያዩታል ይላል» (ዮሐንስ 19፡34፥37)።



## ነቢያት በመሢሑ መሞት ላይ የተናገሩትን በተመለከተ...

መሢሑ ከሀብታሞች ጋር ይቀበራል:

ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ጽፏል:-

> «ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ» (ኢሳይያስ 53፡9)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጸመ።

እንዲሁ፥ ከሰባት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሐዋርያው ማቴዎስ እንዲህ ጽፏል:-

> «በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ። ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፥ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፥...» (ማቴዎስ 27፡57-60)።

## ነቢያት ስለ መሲሑ ትንሣኤ ትንቢትን ተናገሩ. . .

መሲሑ ከሞት ይነሣል፡

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ጽፏል፡-

«ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም» (መዝሙረ ዳዊት 16፡10)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጻሚነት አግኝተዋል።

እንዲሁም፥ ከአንድ ሺ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በትንቢት ተናግሮታል።

«. . .እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል። ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤ ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል» (ሉቃስ 18፡31-33)።

ጴጥሮስ ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ እንዲህ ይላል፡-

«ዳዊት ስለ እርሱ እንዲህ ይላልና፡- «ጌታን ሁልጊዜ በፊቴ አየሁት፥ እንዳልታወክ በቀኜ ነውና። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው፥ ልሳኔም ሐሴት አደረገ፥ ደግሞም ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም።. . . ይህን ኢየሱስ እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤»

(ሐዋርያት ሥራ 2፡25-27፤ 32)።



## መሲሑ በሚጎናጸፈው ክብር ላይ የተነገረ ትንቢት. . .

መሲሑ በእግዚአብሔር ቀኝ ይቀመጣል፡

ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ጽፏል፡-

«እግዚአብሔር ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» (መዝሙረ ዳዊት [110]፡1)።

### በኢየሱስ ጊዜ ተፈጽሞአል

እንዲሁም፥ ከአንድ ሺ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት፡

ኢየሱስ ካረገ በኋላ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎአል፡-

«ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው። ዳዊት ወደ ሰማያት አልወጣምና፥ ነገር ግን እርሱ፡- ጌታ ጌታዬን፡- ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» (የሐዋርያት ሥራ 2፡32-35)።

ሐዋርያው ዮሐንስም በራእይ ከኢየሱስ የተነገረውን እንዲህ ሲል ጽፎታል፡-

«እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደ ተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» (ራእይ 3፡21)።

## ነቢያት መሢሐ በመላ ዓለም ላይ ንግሥናን እንደሚቀዳጅ የተናገሩት ትንቢት...

መሢሐ ወደ ዓለም ይመለሳል:

ነቢዩ ዘካርያስ እንዲህ ጽፏል:-

> እነሆ፥ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል፥ ብዝበዛሽንም በውስጥሽ ይካፈላሉ። እግዚአብሔርም ይወጣል፥ በሰልፍም ቀን እንደ ተዋጋ ከእነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል። በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፤ ደብረ ዘይትም በመካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፥ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል፤...» (ዘካርያስ 14:1፥ 3፥ 4)።

### በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ይፈጸማል:-

ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሉቃስ ከትንሣኤ አርባ ቀን በኋላ እንዲህ ዘግቦአል:-

> «...እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም:- የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው። በዚያን ጊዜ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥» (ሐዋርያት ሥራ 1:9-12)።



## ነቢያት መሢሐ በመላ ዓለም ላይ ንግሥናን እንደሚቀዳጅ የተናገሩት ትንቢት...

መሢሐ በአሕዛብ ላይ በክብር ላይ ክብርን የተጎናጸፈ ንጉሥ ይሆናል:

ነቢዩ ዳንኤል እንዲህ ጽፏል:-

> «በሌሊት ራእይ አየሁ፤ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ ... ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው፤...» (ዳንኤል 7:13፥ 14)።

### በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ይፈጸማል።

እንዲሁም፥ ከ550 ዓመታት በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አለ:-

> «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤» (ማቴዎስ 25:31፤ 32)።

## ነቢያት መሢሐ በመላ ዓለም ላይ ንግሥናን እንደሚቀዳጅ የተናገሩት ትንቢት...

መሢሐ የዘለዓለም ንጉሥ ይሆናል:

ነቢዩ ዳንኤል ከጻፈው ብንጠቅስ:-

> «...ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው» (ዳንኤል 7:14)።

### በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ይፈጸማል።

እንደዚሁ፥ ከ550 ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት:

ሉቃስ፥ መልአኩ ገብርኤል ለማርያም እንዲህ እንዳላት ይዘግባል:-

> «እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥... በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም» (ሉቃስ 1:32፤33)።

## ነቢያት መሢሑ በመላ ዓለም ላይ ንግሥናን እንደሚቀዳጅ የተናገሩት ትንቢት. . .

መሢሑ፤ ራሱ እግዚአብሔር ሆኖ ይነግሣል፡

ነቢዩ ዳዊት የጻፈውን ብንመለከት፡-

«ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ፥ እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እነግራለሁ፤ . . .አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው» (መዝሙረ ዳዊት [(45): 1፥6])።

ነቢዩ ኢሳይያስም እንዲህ ጽፏል፡-

«አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም . . . ኃያል አምላክ, . . . ተብሎ ይጠራል» (ኢሳይያስ 9፡6)።

ነቢዩ ኤርምያስም የጻፈውን ብናይ፡-

«እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥. . . የሚጠራበትም ስም፡- እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው» (ኤርምያስ 23፡5፥6)።

### በኢየሱስ ዳግም ምጽአት ይፈጸማል።

አሁንም ከተወሰኑ መቶ ዓመታት በኋላ እንደ ኢንጅሉ መሠረት፡

በዕብራውያን መልእክት እንዲህ ተጽፏል፡-

«ስለ ልጁ ግን፡ አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘለዓለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው» (ዕብራውያን 1፡8)።



## በቀድሞ ዘመን፥ በነቢያትና በሙሴ መሠረት. . .

### መጨረሻውን ከመጀመሪያ የሚናገር ማን ነው?

ነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔር እንዲህ እንዳለ ጽፏል፡-

«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም። እነሆ፥ የቀድሞው ነገር ተፈጸመ፥ አዲስ ነገርም እናገራለሁ፤ አስቀድሞም ሳይበቅል እርሱን አስታውቃችኋለሁ።

እኔ አምላክ ነኝና፥ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም። በመጀመሪያ መጨረሻውን፥ ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ፤ ምክሬ ትጸናለች ፈቃዴንም ሁሉ አደርጋለሁ እላለሁ።» (ኢሳይያስ 42፡8-9፤ 46፡9-11)።

### ትክክለኛ ነቢይ መፈተኛው ምንድን ነው?

በዚሁ ላይ ሙሴ የሚለው አለው፡-

«በልብህም፡- እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፥ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፥ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።» (ኦሪት ዘዳግም 18፡21-22)።

ነቢዩ ኤርምያስ በበኩሉ የጻፈውን ብንጠቅስ፡-

«ስለ ሰላም የተናገረ ነቢይ፥ የነቢዩ ቃል በሆነ ጊዜ፥ እግዚአብሔር በእውነት የሰደደው ነቢይ እንደሆነ ይታወቃል» (ኤርምያስ 28፡9)።

## እንዲሁም፥ ከምእተ ዓመታት በኋላ እንደ ኢየሱስና እንደ ኢንጅል መሠረት፡

<u>በሁሉም ነቢያት ዘንድ የተነገረለት ማን ይሆን</u>?

ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያቱ እንዲህ አላቸው፡-

> «እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው» (ሉቃስ 24፡25-27)።

ከዚያም በኋላና በሌላ ቦታ ኢየሱስ ለሐዋርያቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፡-

> «ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ... በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል» (ሉቃስ 24፡44-47)።

<u>መሢሐዊው ትንቢት ለማን ነበር የተሰጠው</u>?

ሐዋርያው ጴጥሮስ በኢንጅል ውስጥ እንደጻፈው፡-

> «ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፥ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ፥ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር። ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ» (1ኛ ጴጥሮስ 1፡10-12)።



## ክፍል 3፡- መጽሐፍ ቅዱስ የመሢሑ መሥዋዕትነትን አስመልክቶ እንዳሰፈረው።

በሕግጋተ ሙሴ (ቶራኽ) በነቢያትና በመዝሙረ ዳዊት (ዘቡር) እንደምንመለከተው እግዚአብሔር የመሢሑ መሥዋዕትነት ቀዳሚ ሥዕል ይሆን ዘንድ የራሱን ሕዝብ፥ የእንስሳት መሥዋዕትን ያደርጉ ዘንድ አዟል።

<u>አዳም</u>፡- በቶራኽ (ሕግጋተ ሙሴ) ነቢዩ ሙሴ የጻፈውን ብናነብ፡-

«እግዚአብሔር አምላክ ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም። (ዘፍጥረት 3፡21)።

<u>ኖኅ</u>፡- በቶራኽ ውስጥ የተጻፈውን ብንመለከት፡-

«ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያውን ሠራ፥ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ከንጹሐን ወፎችም ሁሉ ወሰደ፥ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ» (ዘፍጥረት 8፡20)።

2000 ዓመታት ከኢየሱስ በፊት

<u>አብርሃም ይስሐቅ፥ ያዕቆብ</u> ከቶራኽ(ሕግጋተሙሴ)አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ፥ እያንዳንዳቸው ለጌታ የሚሆን የደም መሐውያ እንደሠሩ እናነባለን። (ዘፍጥረት 12፡8፤ 26፡25፤ 46፡

1000 ዓመት ከኢየሱስ በፊት

<u>ዳዊት</u> ፡- በቶራኽ የተጻፈውን ብንጠቅስ፡-

«ዳዊትም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የደኅንነቱን መሥዋዕት አቀረበ፥» (ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21፡26)።

<u>ኢየሱስ</u> ፡ በኢንጅል ውስጥ እንዲህ ተጽፏል፡-

«...አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል።» (ዕብራውያን 9፡26)።

## የደም መሥዋዕት ዓላማና ትርጉም

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቁም። አለመታዘዝ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ኃጢአት ነው። ኢንጅል የአዳም ኃጢአት ያስከተለውን ውጤት ይናገራል።

> «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤» (ሮሜ 5፡12)።

ስለዚህም ለሰው ሁሉ ሞት የተገባ ሆነ፥ ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ዓይን ኃጢአተኛ ነውና።

አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከፈጸሙ በኋላ፥ እርቃናቸውን ለመሸፈን ቅጠላ ቅጠሎችን ሰፉ። ይሁንና እግዚአብሔር ራሱ የመረጠውን አለበሳቸው። የተጻፈውን ከቶራኽ ብናነብ፡-

> «እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው፥ አለበሳቸውም።» (ዘፍጥረት 3፡21)።

ቁርበቱ የታረደ እንስሳ ቁርበት ነበረ። ስለዚህ ለኃጥአን ቤዛ ይሆን ዘንድ የንጹሑን ደም የማፍሰስን መርሕ ለዓለም ያስተዋወቀ ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ እንገነዘባለን።

በኋላም እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ነግሮታል፡-

> «የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት» (ዘሌዋውያን 17፡11)።

ኢንጅልም ይህንኑ ደግሞ በመጻፍ እንዲህ ይላል፡-

> «. . .ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብራውያን 9፡22)።

ነገር ግን ኢንጅል እንዲህ ደግሞ ይላል፡-

> «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም። የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና። አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል።. . . የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም» (ዕብራውያን 10፡1፥ 4፤ 9፡26፥12)።



በዚሁ ምክንያት ኢየሱስ፡-

> «የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በመባል ይታወቃል (ዮሐንስ 1፡29)።

## በቶራኽ ውስጥ የእግዚአብሔር በግ መሥዋዕት ይሆን ዘንድ የተነገረ ትንቢት. . .

የተጻፈውን ከቶራኽ ስናነብብ እንዲህ ይላል፡-

> «ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፥ እንዲህም አለው፡- አብርሃም ሆይ። አብርሃምም፡-እነሆ፥ አለሁ አለ። የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፤ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ» (ዘፍጥረት 22፡1-2)።

በቶራኽ ውስጥ ያለው ዜና መዋዕል ካልዕ 3፡1 የሞሪያም ተራራ ማለት ከነቢዩ አብርሃም ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ፥ ንጉሥ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ የሠራበት ቦታ መሆኑን ይገልጻል። እግዚአብሔር የመረጠላቸውን ቦታ ለመድረስ ትንሽ ሲቀራቸው ልጁ ለአባቱ ለአብርሃም የተናገረውን ቶራኽ መዝግቦት እናገኛለን፡-

> «አባቴ ሆይ . . .እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው? አለ። አብርሃምም፡- ልጄ ሆይ፥

1) <u>የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል</u> አለው፤ ሁለቱም አብረው ሄዱ። እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ፤ አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ፥ እንጨትም ረበረበ፤ ልጁን ይስሐቅንም አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ አጋደመው። አብርሃምም እጁን ዘረጋ፥ ልጁንም ያርድ ዘንድ ቢላዋ አነሣ። የእግዚአብሔር መልአክም ከሰማይ ጠራና፡- አብርሃም አብርሃም አለው፤ እርሱም፡- እነሆኝ አለ። እርሱም፡- በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ። አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ

በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።

2) አብርሃምም ያንን ቦታ ያህዌ ይርኤ ብሎ ጠራው፤ እስከ ዛሬም ድረስ በእግዚአብሔር ተራራ ይታያል ይባላል። የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው፥ እንዲህም አለው፡- እግዚአብሔር፡- በራሴ ማልሁ ይላል፤

3) የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና» (ዘፍጥረት 22:7-16፤ 18)።

ምንም እንኳ አብርሃም በሞሪያ ተራራ ያቀረበው መሥዋዕት ጠቦት አይሁን እንጂ ያቀረበው ተባዕት በግ እግዚአብሔር ለዓለም በረከት ሲል የሚያቀርበው ጠቦት ቀዳሚ አምሣል ነው።

## እንደ ኢንጅሉ መሠረት፡- በኢየሱስ ተፈጻሚነትን አገኘ።

ቀደም ሲል የተመለከትናቸውና የተሠመሩባቸው ሦስቱም ትንቢቶች መፈጸማቸውን በሚመለከት የሚያሳዩ ነጥቦች እነሆ፡-

1) ከነቢዩ አብርሃም ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ መጥምቁ ነቢዩ ዮሐንስ ኢየሱስን ባየው ጊዜ እንዲህ አለ፡-

«እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ » (ዮሐንስ 1:29)።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ሐዋርያው ዮሐንስ በታየው ራእይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ እንደ ሆነ ተመልክቷል። ይህንን ከኢንጅል ብንመለከት፡-

«ታርደሃልና፥ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ...» (ራእይ 5:9)።

ስለዚህ ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢአት ያስወግድ ዘንድ ሕይወቱን መሥዋዕት ያደረገ የእግዚአብሔር በግ ነው።

2) ማቴዎስም ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት የመዘገበውን ብንመለከት፡-

«ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር» (ማቴዎስ 16:21)።



3) ሐዋርያው ጳውሎስ ለዓለም የተገባው የበረከት ቃልን በተመለከተ በኢንጅል ከጻፈው ብንጠቅስ፡-

«መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ።» (ገላትያ 3:8)።

የተስፋ ዘርን በተመለከተ፡

ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈውን ስናይ፡-

«ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፡- ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፡- ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ» (ገላትያ 3:16)።

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአሕዛብ ሁሉ የተሰጠ የተስፋ ቃል መሥዋዕት በሆነው በእግዚአብሔር በግ፥ ከአብርሃም ዘር በሆነው፥ በመሲሑ ኢየሱስ በማመን የሚገኝ መዳን ነው።

## ክፍል 4፡- በአሁኑ ጊዜ ለአንተና ለአንቺ የሚሆን የመሢሑ በረከት

ውድ አንባቢ፥ እንደ ኢንጅሉ መሠረት ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-

«አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው» (ዮሐንስ 6:37-40፥ 47)።

እንዲሁም፥ ኢንጅል እንዲህ ሲል ያረጋግጥልሃል፡-

«ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1:15)።

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥

እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥» (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4-6)።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፥» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።

ልታስታውሰው የሚገባህ፡-

መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህና እንደ ጌታህ ትቀበለው ዘንድ እግዚአብሔር ፈቃዱ ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ በተቀበልህ ጊዜ ለኃጢአትህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም የሰማያዊ አባትህ እንደሆነ ታስተውላለህ። መንግሥተ ሰማይም የምትገባበት ዋስትና ይኖርሃል። መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ከተቀበልክ የሚከተለውን ጸሎት ልትጸልይ ዘንድ ትችላለህ፤ እግዚአብሔርም ይሰማሃል።

ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ መሢሑ ኢየሱስን ወደ ዓለም ስለላክኸው አመሰግንሃለሁ። ለእኔ ያለህን ፍቅር በመሢሑ ኢየሱስ ስለገለጽክልኝ አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ስርየት ይሆን ዘንድ መሢሑ ኢየሱስ ሕይወቱ በመስቀል ላይ እንዲያልፍ ስላደረግህ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለም ሕይወት ይኖረኝም ዘንድ ኢየሱስን ከሞት ስላስነሣህ አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ፤ ኃጢአቴንም ሁሉ ይቅር ትለኝ ዘንድ እሻለሁ። ለእኔ ሲል ሕይወቱን አሳልፎ በሰጠው፥ በመሢሑ ኢየሱስ ያገኘሁትን የኃጢአት ሥርየት በዚችው ደቂቃ እቀበላለሁ። መሢሑ ኢየሱስ ጌታዬ ይሆን ዘንድ ፈቃዴ ነው። ኢየሱስ የሚወዳቸውን ያህል እኔ ደግሞ ሌሎችን ሁሉ እወድ ዘንድ እርዳኝ። ኃጢአቴን ሁሉ ስለተሸከምክ አመሰግንሃለሁ። ስለተቀበልከኝም አመሰግንሃለሁ። ይህን ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ፥ አሜን።